# አውሮራ ጎዳና (Aurora Ave) ፕሮጀክት


የማዳረስ ማጠቃለያ

Seattle Department of Transportation

2024

## ምን እየተደረገ ነው ያለው?

የAurora Ave ፕሮጀክት Aurora Ave N ደህንነቱ የተጠበቀ እና ለሁሉም ሰው ለመጠቀም ቀላል እንዲሆን ይፈልጋል። ያንን ለማድረግ፣ እዚህ የሚኖሩ ሰዎችን፣ ንግዶችን የሚያንቀሳቅሱ እና የሚራመዱ፣ በእግር የሚሄዱ፣ የሚያንከባልሉ እና በመንገድ ላይ የሕዝብ መጓጓዣ የሚወስዱትን እያዳመጥን ነው። ፀደይ 2024 ውስጥ፣ በAurora Ave N. ላይ ከማህበረሰቦች ጋር ለመጋራት ረቂቅ የንድፍ ሀሳቦችን አዘጋጅተናል። ይህ ማጠቃለያ በዚያ ሂደት ውስጥ የሰማነውን ይናገራል። ግባችን የድጋፍ ገንዘብ ሲኖረን እነዚህን ማሻሻያዎች ለማድረግ ነው።




## እርስዎ ምን ማድረግ ያስፈልግዎታል?

እኛ በፕሮጀክቱ አካባቢ ከሚኖሩ፣ ከሚሰሩ እና በዚያ ውስጥ ከሚያልፉ ሰዎች የሰማነውን እያካፈልን ነው። እንዲሁም እኛ በዚህ ፕሮጀክት የወደፊት ስራ ውስጥ እርስዎ መሳተፍ እንዲችሉ በቀጣይ ምን እንደምናደርግ እንዲያውቁ እንፈልጋለን። እርስዎ እንዴት እንደተገናኙ መቆየት እንደሚችሉ ለማወቅ የእኛን ማጠቃለያ የመጨረሻ ገጽ ይመልከቱ።

## ለዚህ Aurora Ave ፕሮጀክት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

Aurora Ave N/State Route 99 በሲያትል ውስጥ በጣም ከተጨናነቁ መንገዶች አንዱ ነው። የተለያዩ አይነት ሰዎች እና የንግድ ስራዎች ባሉባቸው ሰፈሮች ውስጥ ያልፋል። RapidRide E Line የሕዝብ አውቶቡስ Aurora Ave N ይጠቀማል፣ እና ደግሞም ይህ መንገድ ጭነትን ለማንቀሳቀስ ጠቃሚ ነው። መንገዱ ብዙ ቤቶች፣ ሱቆች፣ አገልግሎቶች፣ እና ስራዎችን ይገናኛል። ነገር ግን ብዙ ግጭቶች፣ ከእግረኛ መንገዶች ጋር ችግሮች ነበሩ፣ እና የመንቀሳቀስ ችግሮች ላለባቸው ሰዎች ወዲህ ወዲያ ለማለት ቀላል አይደለም። እኛ ለAurora Ave N ደህንነት፣ ተንቀሳቃሽነት፣ እና ለሁሉም ሰው ተደራሽነትን የሚያሻሽል አብረን አዲስ ራዕይ ለማድረግ እየሰራን ነው።

## በAurora Ave ፕሮጀክት ውስጥ የሚሳተፉ ተወካይ ድርጅቶች እነማን ናቸው?

የ Aurora Ave ፕሮጀክት በሲያትል የመጓጓዣ መምሪያ (SDOT) እና በኪንግ ካውንቲ ሜትሮ እየተደረገ ያለ የቡድን ጥረት ነው። እኛ በ2021 ከተቀበልነው ከዋሽንግተን ስቴት የመጓጓዣ መምሪያ (WSDOT) የእግረኛ እና የብስክሌት ፕሮግራም የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ ከተቀበልነው የድጋፍ ገንዘብ እየተጠቀምን ነው። እንዲሁም በተጨማሪ ሲያትል እና ኪንግ ካውንቲ ሜትሮ ለማንቀሳቀስ ከሚሰበሰበው ቀረጥ የእርዳታ ገንዘብ ድጋፍ አለን።

## የማዳረስ የጊዜ ሰሌዳ

- **በጋ/ በልግ 2022** የዳሰሳ ጥናት #1 ለማህበረሰብ አባላት ቁልፍ ስጋቶች የሆኑትን እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለመረዳት
- **ጸደይ/ በጋ 2023** የዳሰሳ ጥናት #2 ማህበረሰቡ የAurora Aveን የመጓጓዣ ተግዳሮቶችን ለማስተካከል ምን አይነት የንድፍ ለውጦችን ማየት እንደሚፈልጉ ለማወቅ

  በአካባቢው የህዝብ መጓጓዣን ጨምሮ፣ የማህበረሰብ አውደ ጥናቶች ስለ Aurora Ave የወደፊት ራዕይ እና ንድፍ እቅዶችን ለመፍጠር
- **ጸደይ 2024** ረቂቅ የንድፍ ፅንሰ ሀሳቦችን እና የግምገማ መስፈርቶችን ከማህበረሰቡ ጋር ይጋሩ

  የዳሰሳ ጥናት # 3 ረቂቅ ንድፎቹ ቀደም ባሉት ደረጃዎች የሰማነውን የAurora Ave የሃሳብ ርቀቶች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች የተካተቱ ስለመሆኑ ከማህበረሰብ አስተያየት ለማግኘት

## የማዳረስ ዘዴዎች

የመስመር ላይ፣ የፖስታ መላላክ እና በአካል የመገኘትን በማጣመር ከAurora Ave ፕሮጀክት ጋር በፀደይ 2024 ከ9,600 በላይ ሰዎች ተሳትፈዋል። ከዚህ ባለፈ፣ ለዚህ ፕሮጀክት በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ከ430,000 በላይ እይታዎች ነበሩን። ቢያንስ ሰዎችን በ148 ዚፕ ኮድ ውስጥ ደርሰናል/ አግኝተናል።

**የመስመር ላይ እና በፖስታ መላላክ ማዳረስ:**

- በመስመር ላይ የዳሰሳ ጥናት 8,646 ሰዎችን ደርሷል
- የመድብለ ባህላዊ ሚዲያ እና ዲጂታል ማስታወቂያዎች 3,745,514 ግንዛቤዎች ነበሯቸው
- ፖስትካርድ መላላኪያ ለ14,700 ሰዎች ተልኳል
- የድር ዝመናዎች እና የፕሮጀክት ኢሜይል በlistserv በ19,740 ሰዎች ታይቷል
- በPeachjar በራሪ ወረቀቶች በኩል በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ለ7,310 ሰዎች ተልኳል
- የፕሮጀክት ኢሜይል ገቢ መልእክት ሳጥን 30 ኢሜይሎች አግኝቷል
- የብሎግ ልጥፎች እና ማህበራዊ ሚዲያዎች 441,700 ሰዎች ደርሰዋል
- ምናባዊ ክፍት ቤት 40 ሰዎች ደርሷል
- የኪንግ ካውንቲ ሜትሮ የሕዝብ መጓጓዣ ማስጠንቀቂያዎች 10,438 ሰዎች ደርሰዋል

**በአካል ለተገኙ ማዳረስ:**

- በአካል በመገኘት ክፍት ቤቶች 90 ሰዎች ደርሰዋል
- ከቤት ወደ ቤት ለ285 ንግዶች ተዳርሷል
- ከ120 በላይ ሰዎች ጋር አንድ ለአንድ የተደረገ ማዳረስ እና ውይይት
- ከ16 ድርጅቶች እና ቡድኖች ጋር የባለድርሻ አካላት ገለጻዎች



## እስካሁን የሰማነው

ጸደይ 2024 ውስጥ፣ ከ9,600 በላይ በAurora Ave N የሚኖሩ፣ የሚሰሩ፣ ወይም የሚጓዙ ወይም በአቅራቢያ ያሉ ሰዎች ከኛ ጋር ተሳትፈዋል። እኛ በመስመር ላይ እና በአካል ለሰዎች በብዙ መንገዶች ግብረ መልስ እንዲያካፍሉ እድሎችን ሰጥተናል። ይህ ፈጣን ማጠቃለያ ነው፣ እና እርስዎ ተጨማሪ ዝርዝሮችን በ2024 ድህረ-ገፃችን ላይ ባለው የማዳረስ ዘገባ ላይ ማንበብ ይችላሉ።

**ብዙ ሰዎች ሃሳቦቻቸውን እና ግብረ መልሶቻቸውን ቢያንስ በአንዱ ረቂቅ የንድፍ ሀሳቦች ውስጥ ተወክለው አይተዋል።**

- የዳሰሳ ጥናት ከተደረጉት ሰዎች መካከል 60% የሚሆኑት ሃሳቦቻቸው በረቂቁ የንድፍ ሀሳቦች ውስጥ እንደተወከሉ ተሰምቷቸዋል
- 10% ያህሉ ሃሳቦቻቸው እንደተወከሉ አልተሰማቸውም
- 30% ያህሉ እርግጠኛ አልነበሩም

የተሻሉ የእግረኛ መንገዶችን፣ ብዙ መሻገሪያዎች፣ መብራት እና የመሬት አቀማመጥ ሥራዎችን ጨምሮ አንዳንድ ሃሳቦች ከሁሉ ይልቅ በአብዛኛዎቹ ተደግፈዋል። ነገር ግን፣ ሰዎች ስለ ብስክሌት መስመሮች እና የአውቶቡስ መስመሮች የተለያየ አስተያየት ነበራቸው።







## ስምምነት ያየንበት

በዳሰሳ ጥናቱ ባለብዙ ምርጫ ክፍል ውስጥ ከተካፈሉት ባህሪያት እና ሃሳቦች ውስጥ፣ በአለም አቀፍ ደረጃ ከሁሉ ይልቅ የተወደዱ በርካቶች ነበሩ። ከ 70% በላይ የሚሆኑ የዳሰሳ ጥናት ያደረጉ ሰዎች እነዚህን ባህሪያት ደግፈዋል:-

- ለመንገድ እና በእግር ለሚሄዱ ሰዎች የተሻለ መብራት
- በእግር ለሚሄዱ፣ ቢስክሌት ለሚጋልቡ እና የሚያንከባለሉ ሰዎች ደህንነቱ የተጠበቀ የእግረኛ መንገድ
- የአውቶቡስ መጠለያዎች
- የመሬት አቀማመጥ ሥራ እና ዛፎች

ከ50 - 60% አካባቢ ድጋፍ በማግኘት፣ የተሻለ ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶች፣ አረንጓዴ አማካዮች፣ እና በመንገዱ መካከል ያሉት ከፍ ያሉ መስመሮች በመጠኑ ያነሱ ተወዳጅ ነበሩ።

## አለመግባባትን ያየንበት

74% ያህል የሚሆኑ አስተያየቶች ስለ ተሽከርካሪ መስመር ውቅር፣ የብስክሌት እና የአውቶቡስ መዳረሻ፣ እና የአውቶቡስ እና የብስክሌት መሠረተ ልማት ነበሩ።

ከሁሉ ይልቅ በጣም ከፋፋይ የሆኑት ባህሪያት "አሁን ያሉ ነባር የተሽከርካሪ መስመሮችን ቁጥር ማቆየት" እና "የመሃል አውቶብስ ብቻ መስመሮች" ነበሩ። ወደ 40% ያህል የሚሆኑ የማህበረሰብ አባላት እነዚህን ባህሪያት ወደውታል እና 40% እነሱን አልወደዷቸውም። እነዚህ ሁለት ባህሪያት ደግሞ የተገላቢጦሽ ግንኙነት ነበራቸው፤ አንዱን የወደዱ ቡድኖች፣ ሌላውን አልወደዱም። የሰማነው አንዳንድ/ ጥቂት ክርክሮች እነሆ፤

### የተሽከርካሪ መስመር ውቅር፤

*"ለንግድ ሥራ ለንግዶች ተደራሽነት የጭነት ተንቀሳቃሽነት በተገቢው ተይዘው መቆየት በጣም አስፈላጊ ነው።"*

*"ይህ ክፍል በከፍተኛ ፍጥነት በሚሽከረከሩ ተሽከርካሪዎች እና በጥሩ ሁኔታ ባልተያዙ መንገዶች የተጐሳቆለ የማህበረሰብ የንግድ ማዕከል ነው።"*

*"እኔ የትራፊክ መስመሮቹ ወደ አንድ መስመር ተቀንሰው እና ለእግረኛ/ ንግድ አገልግሎቶች ጠቄሜታ የሚውለውን ቦታ (ለምሳሌ ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮች) ማየት እመርጣለሁ።"*

*"ቢያንስ 2 አጠቃላይ ዓላማ ያላቸው መስመሮችን በእያንዳንዱ አቅጣጫ ማስቀመጥ ለማንኛውም ንድፍ ቅድመ ሁኔታ መሆን አለበት። ያለበለዚያ የተቆላለፈ፣ ብክለት የሚፈጥር ይሆናል[from slow moving traffic]፣ እና በአጎራባች መንገዶች ላይ የትራፊክ መጨናነቅ ይጨምራል..."*

### የአውቶቡስ ብቻ መስመሮች እና የመሃል አውቶቡስ ብቻ የሚሄድበት መስመሮች፤

*"የባሰውን አሽከርካሪዎች ወደ አውቶቡስ መስመሮች እንዲለውጡ ከማበረታታት፣ ከሚጠመዘዙ ተሽከርካሪዎች ጋር ያልተጋሩ ለአውቶቡስ መስመሮች ብቻ የተሰጡ መስመሮች የአውቶቡስ ፍጥነትን ያሻሽላሉ።"*

*"ለአውቶቡስ ብቻ መስመር እጅግ በጣም ጥቂት አውቶቡሶች ብቻ ነው ያሉ።"*

*"በመሃል የሚሄደው የሕዝብ መጓጓዣ ለአውቶቡስ አገልግሎት በጣም ፈጣኑ ከሆነ፣ እንደዚያ አድርጉት! አውቶቡስ የሕዝብ መጓጓዣን ተመራጭ አሰራር አድርጉት!"*

*"መሃል የአውቶቡስ መሄጃ መስመሮች መንገድ መሻገር ላይ ያለውን አደገኛ ልምድ መፍትሄ እንዲያገኝ ብዙ ያስኬዳል።"*

*"የመሃል አውቶቡስ መስመር ሀሳብ ብዙ የእግረኛ መንገድ መሻገር ጥሰት የሚያበረታታ እና የእግረኛ-ተሽከርካሪ አደጋን የሚጨምር መጥፎ ንድፍ ነው።"*

### የብስክሌት መስመሮች፤

*"ከተሽከርካሪ ትራፊክ ይልቅ ለእግረኛ/ ብስክሌት መዳረሻ እና ደህንነት ቅድሚያ ይሰጥ።"*

*"እኔ ራሴ ብስክሌተኛ ነኝ፣ እና በቀጥታ አውሮራ (በጣም ስራ የበዛበት ነው) ላይ ከመጨመር ይልቅ የብስክሌት መንገዶችን በትይዩ ጎዳናዎች ላይ ማከል የተሻለ ይመስለኛል።"*

*"የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ብዙ ሰዎች የኩርባ ዳር አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው አሉ። የተጠበቁ/ የተከለከሉ የብስክሌት መስመሮች ለአረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለተጎዱ፣ በጣም ትናንሽ ልጆች ላሏቸው ወላጆች፣ ወዘተ አደገኛ ሁኔታ ይፈጥራሉ።"*

ሰዎች ስላጋሩት ነገር የበለጠ ለማወቅ የእኛን የማዳረስ ዘገባ ዝርዝር ያንብቡ።

### እንዳያመልጥዎ !

ስለ እኛ የማዳረስ ዝርዝር ዘገባ በእኛ ድህረ ገፅ ላይ ማግኘት ይችላሉ። የማዳረስ ሪፖርቱ እና የፕሮጀክት ድረ-ገጽ በእንግሊዝኛ ብቻ ናቸው።

ይህንን ማጠቃለያ በአማርኛ፣ በቻይንኛ፣ በኮሪይኛ፣ በስፓኒሽ እና በታጋሎግ ቋንቋዎች በእኛ ድህረ ገፅ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

ስለ Aurora Ave ፕሮጀክት እና ስለእኛ ማዳረስ፣ የተተረጎመ መረጃ ለማግኘት እባክዎን (206) 905-3620 ይደውሉ።

በዚህ ፕሮጀክት ላይ ወቅታዊ ሆነው ለመቆየት፣ ለኢሜይል ዝመናዎች ይመዝገቡ እና የእኛንድህረ ገፅ ይጎብኙ። ጥያቄዎች ወይም አስተያየቶች ካልዎት፣ እባክዎን በ (206) 905-3620 ወይም aurorastudy@seattle.gov ያግኙን።

**በእርስዎ ካሜራ የእኛን የፕሮጀክት ድህረ ገጽ ጣቢያ ለመጎብኘት የQR ኮዱን ይቃኙ።**

### የፕሮጀክት መገናኛ፤

ጁልስ ፖሳዳስ (Jules Posadas)፣ የህዝብ ተሳትፎ መሪ
aurorastudy@seattle.gov | 206-905-3620
www.seattle.gov/transportation/auroraproject